# በቪክቶሪያ የተግባረ ትምህርት ምስክር ወረቀት/VCAL ምን'ድር ነው?

## ይህ 11ኛ እና 12ኛ ክፍል ለሚማሩ ተማሪዎች በቀላሉ ማግኘት የሚችሉት የምስክር ወረቀት ይሆናል።

VCAL ፕሮግራም ከሥራ ጋር የተያያዘ ልምድ የሚሰጥ ሲሆን የማንበብና መጻፍ እንዲሁም የቁጥር ትምህርት ችሎታን በማሻሻል ለኑሮና ለሥራ ጠቃሚ የሆነ ችሎታን ለማካበት ይረዳል ማለት ነው። ይህ የምስክር ወረቀት/VCAL ልክ እንደ ቪክቶሪያ ትምህርት የምስክር ወረቀት (VCE) ተቀባይነት ያለው ሙያ ይሆናል።

የVCAL ምስክር ወረቀት ያላቸው ተማሪዎች ብዙ ጊዜ የቴፍ/TAFE፣ የአፕረንቲሽፕ ስልጠና ለማካሄድ ፍላጎት ሲኖራቸው፣ ወይም የመደበኛ ት/ቤት ካጠናቀቁ በኃላ በቀጥታ ሥራ ይጀምራሉ። ስለዚህ የVCAL ትምህርት ከጀመሩ እና ከዚያ በኃላ ግን VCE ለመውሰድ ትክክለኛ ምርጫ ነው ብለው ካመኑበት ሃሳብዎን በመቀየርዎ ዘገየ ማለት አይደለም። የVCAL ትምህርት በሚወስዱበት ጊዜ የሚያጠናቅቋቸው ክፍሎችን ወደ ሌላ የምስክር ወረቀት ሥልጠና ፕሮግራም ለማስተላለፍ ከወሰኑ ያገኙት ውጤት እንደ የVCE ክፍል ሊቆጠር ይችላል።

የVCAL ፕሮግራም ሲማሩ መቀያየር ስለሚችሉ ለርስዎ እንዳመቹና የትምህርት ፍላጎትዎ ማጣጣም ይችላሉ። ከዚህ በታች ላሉ አራት ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት ያላቸው ክፍሎች ተመርጠዋል:

- የማንበብና መጻፍ እንዲሁም የቁጥር ችሎታ
- ከሥራ ጋር በተዛመደ ችሎታ
- ከኢንዱስትሪ ጋር በተዛመደ ለየት ያለ ችሎታ
- የግለሰብ የእድገት ችሎታ

የVCAL ትምህርት በጥሩ ሁኔታ ካጠናቀቁ የምስክር ወረቀት ይሰጥዎታል እንዲሁም ስለተገኘው ውጤትና ስለአጠናቀቁት የትምህርት ዓይነት የሚገልጽ ፅሁፍ ይሰጥዎታል።

## ምን ማወቅ እንዳለብኝ

## የVCAL ትምህርት ለምን'ድር ነው መምረጥ ያለብኝ?

በዩኒቨርሲቲ ትምህርት መቀጠል ለሚፈልጉ ተማሪዎች በVCE መሳተፍ ጥሩ ምርጫ ይሆናል። ይሁን እንጂ ይህ ትክክለኛ ምርጫ መስሎ ላይታይዎት ይችላል።

VCAL ተቀባይነት ያለው እና በ11ኛ እና በ12ኛ ክፍል የሚሰጥ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ችሎታ ይሆናል። ይህም በእጅ ሙያ ትምህርት የተመሠረተ ሲሆን እንዲሁም "የተግባር ትምህርት" ብሚል ስም ይጠራል።

የVCAL ትምህርት ለመውሰድ ከመረጡ "ለሥራ ብቁ የሚያደርግ" የሙያ ችሎታ ልምድ ያገኛሉ እንዲሁም የሚያገኙት ችሎታ በቴፍ/TAFE ወይም በሥራ ቦታ ላይ በበለጠ ሥልጠና እንዲያገኙ ይረዳዎታል።

## መቸ ነው የVCAL ትምህርት መውሰድ የምችለው?

በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት 11ኛ ወይም 12ኛ ክፍል ሲማሩ የVCAL ፕሮግራም መጀመር ይችላሉ። እንዲሁም የVCAL ትምህርት በአብዛኛው የቴፍ/TAFE ተቋማትና በአንዳንድ የጎልማሶች ማህበረሰብ ትምህርት (ACE) ማእከላት በኩል ይቀርባል።

## የVCAL ትምህርት ደረጃዎች ምንድን ናቸው?

VCAL ሶስት ደረጃዎች ሲኖሩት፤ እነሱም ጀማሪ/መሰረታዊ፤ መካከለኛ እና የበላይ/ከፍተኛ ደርጃዎች ናቸው። ለርስዎ በሚመጣጠን አቅምና ፍላጎት መሠረት የVCAL ደረጃ መጀመርና ማጠናቀቅ ይቻላል።

## ለመጀመር የሚያስፈልግ ቅድመ ሁኔታ አለው ወይ?

የለውም፤ በርስዎ አቅም በፈቀደው VCAL ደረጃ መጀመር ይችላሉ። ለርስዎተስማሚ በሆነው ደረጃ ላይ ውሳኔ እንዲሰጡበት በአስተማሪዎ ወይም የክንክን ሰጪ አማካሪዎ በኩል እርዳታ ያገኛሉ።

## የVCAL ለመጨረስ ምን ያህል ጊዜ ይወስድብኛል?

የVCAL ትምህርት ለ11ኛ እና 12ኛ ክፍል ተማሪዎች ትብሎ የወጣ ነው። ይህን ፕሮግራም በሚገባ ሲያጠናቅቁ የVCAL ምስክር ወረቀትና ስላጠናቀቁት ደረጃ ውጤት የሚገልጽ የፅሁፍ ሪፖርት ማግኘት ይችላሉ።

## የVCAL በሚገባ ካጠናቀቁ በኃላ ምን ያገኛሉ?

የVCAL ፕሮግራም እንደርስዎ ምርጫ መሠረት ማለት ለመሰረታዊ፤ ለመካከለኛ እና ለከፍተኛ ደረጃ ትምህርቱን በሚገባ ካጠናቀቁ በኃላ የVCAL ምስክር ወረቀት ይሰጥዎታል። እንዲሁም ሁሉንም የVCAL, VCE እና VET ክፍሎች ዝርዝር ውጤት የሚገልፅ ፅሁፍ ማግኘት ይችላሉ።

## የVCAL ትምህርት የት መውሰድ እችላለሁ?

ይህ ትምህርት በአገር አቀፍ በት/ቤቶች፣ ቴፍ/ TAFE ተቋማት እና በአንዳንድ የጎልማሶች ማህበረሰብ ትምህርት/ACE ማእከላት በኩል ይሰጣል። የVCAL ትምህርት አቅራቢዎችን ዝርዝር ለማግኘት በዌብሳይት www.vqa.gov.au ላይ ይመልከቱ።

## የእኔ VCAL መማር ምን ዓይነት ዋጋ ይኖረዋል?

## የሙያ ትምህርትና ሥልጠና ምስክር ወረቀት(VET) ምን’ድር ነው?

የVET ፕሮግራም በመውሰድ በት/ቤቶች፣ በስልጠና ተቋማት እና ተማሪዎች በበለጠ ለሥራ እንዲዘጋጁ ሥልጠና ለማግኘት በኢንዱስትሪዎች ላይ ለመሳተፍ እድሉን ይከፍታል። አብዛኛው ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የVET ኮርሶችን በመስጠት ለVCAL ትምህርት አስፈላጊ የሆኑ ነጥቦችን በሚገባ ለማጠናቀቅ የሚያስችልና በአገር አቀፍ ተቀባይነት ያለው የሙያ እውቅናን ይሰጣል።

## ይህ በእኔ VCAL ላይ አስተዋፆ/ዋጋ ይኖረዋልን?

አወ፡ እንዲሁም ቀደም ሲል ምን ያህል የVCAL ነጥብ እንዳለዎትና ለወደፊት ለሚያካሂዱት የVCAL ፕሮግራም ምን ያህል ነጥብ እንደሚቀርዎት ለአስተማሪዎ ወይም ለእንክብካቤ ሰጪ አማካሪዎ መጠየቅ ያስፈልጋል።

## በ VCE የሚሰጠውን የትምህርት ዓይነት ወስጃለሁ። በምወስደው የVCAL ላይ ይቆጠራል ወይ?

አወ፣ ውጤትዎ 'S' ከሆነ ማለት የVCE ክፍልን በጥሩ ሁኔታ ካጠናቀቁ በሚወስዱት የ VCAL ትምህርት ነጥብ ይኖረዋል። ለወደፊት ለሚያቅዱት የVCAL ፕሮግራም ምን ያህል ነጥብ እንደሚቀርዎት ለአስተማሪዎ ወይም ለእንክብካቤ ሰጪ አማካሪ መጠየቅ ይኖርብዎታል።

## ሃሳቤን ከቀየርኩ ወደ VCE መቀየር እችላለሁ ወይ?

አወ፣ ሃሳብዎን ከቀየሩና ወደ VCE መለወጥ ከፈለጉ ወይም የVCAL ትምህርት ካጠናቀቁ በኃላ በVCE መጠየቅ ከፈለጉ ታዲያ በሚገባ ያጠናቀቁት ማንኛውም የVCE ክፍሎች እንደ µ≠d VCAL ክፍል በመቁጠር በሚወስዱት የVCE ፕሮግራም ላይ ነጥብ ይሰጠዋል። በተጨማሪ በVCAL ትምህርት ላይ ያጠናቀቁትን ክሬዲት/ነጥብ ወደ ሌላ ክፍልና አካል ማዛወር ይችሉ ይሆናል። ይህንን አማራጭ ለመውሰድ ከአስተማሪዎ ወይም ከእንክብካቤ ሰጪ አማካሪ ጋር መወያየት ያስፈልጋል።

## በVCAL ተመዝግቤ እያለሁ የትርፍ ሰዓትና/ወይም የአፕረንትስሺብ ሥራ መቀጠል እችላለሁ ወይ?

በVCAL ትምህርት ላይ ከተመዘገቡ የትርፍ ሰዓት ለመሥራት የተቀባይነት ድጋፍ ማግኘት ይችላሉ። ይህ ሥራ እንደሚከተለው ያካተተ:

- የትርፍ ሰዓት አፕረንትስሽፕስ ወይም ትሬኒሽፕ ሥልጠና
- የትርፍ ሰዓት ሥራ
- በሥራ ቦታ ላይ የሚተካ

## VCAL እንዴት ይገመገማል?

VCAL ተቀባይነት ካገኘ የምስክር ወረቀት የተቀናጀ ትምህርት ነው። እያንዳንዱ የትምህርት ፕሮግራም እንደ ፕሮግራሙ አስፈላጊነት ይገመገማል።

## ለጠቅላላ ግኝት/መግቢያ ፈተና/ GAT መቀመጥ ያስፈልገኛልን?

ይህ ፈተና በጽሁፍ፣ በሂሳብ ትምህርት፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ በሰባዓዊና ማህበራዊ ሳይንስና ስነ-ጥበብ ያለዎትን እውቀትና ችሎታ የሚመዝን ይሆናል። በክፍል 3 እና 4 በተከታታይ ለሚማሩ የVCE ተማሪዎች በሞላ የሚወሰድ ይሆናል። ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ ተማሪዎች የ VCE VET ክፍል 3-4 በተከታታይ የሚወስዱ ከሆነ በGAT ፈተና ላይ መቀመጥ ይኖርባቸዋል። በVCAL ክፍል ብቻ ለተመዘገቡ ተማሪዎች የGAT ፈተና መውሰድ ግዴታ አይደለም። ይሁን እንጂ ለወደፊት ትምህርት፣ ሥልጠና ወይም ሥራ ለመግባት ትክክለኛ መንገድ ከሆነ የGAT ፈተናን ለመውሰድ መምረጥ ይችላሉ።

## ምን'ድር ነው የማጠናው?

ከአስተማሪዎ ወይም ከአማካሪዎ በሚያገኙት እርዳታ መሰረት የርስዎን የትምህርት ፍላጎትና ተስማሚነት የሚያሟላ የVCAL ፕሮግራም መምረጥ ይችላሉ። መወሰድ ካለባቸው አራት የVCAL ክፍሎች ውስጥ መምረጥ ይችላሉ:

### ክፍል/Strand 1 - የማንበብና መጻፍ እንዲሁም የቁጥር ችሎታ

የVCAL ፕሮግራምዎ የማንበብና መጻፍ እንዲሁም የቁጥር ትምህርት ዓይነት ያካተተ መሆን አለበት። እነዚህም ከVCAL የማንበብና መጻፍ ችሎታና ከVCAL ቁጥር ትምህርት ችሎታ ክፍል ውስጥ የተመረጡ ሲሆን እንዲሁም ከVCE የእንግሊዝኛና ሂሳብ ትምህርት ወይም ከሌሎች ከፍተኛ ትምህርት ማለት እንደ የአጠቃላይ የትምህርት ምስክር ወረቀት (ለአዋቂ ሰው) የሚሰጥ ኮርስ ሲሆን ይህም በቴፍ/TAFE ተቋማትና በጎልማሶች/ACE ማእከላት የማንበብና መጻፍ እንዲሁም የቁጥር ትምህርት በማቅረብ ለሙያ ማሻሻያና ወደ ሥራ መስክ ለመግባት የሚጠቅሙ ችሎታዎችን ለማጠናከር ይረዳል።

### ክፍል/Strand 2 - ከኢንዱስትሪ ጋር በተዛመደ ለየት ያለ ችሎታ

የርስዎ የVCAL ፕሮግራም ትምህርት ከVET ወይም ከVCE VET ፕሮግራም ውስጥ የኢንዱስትሪ ክፍል የሚለውን ዓርእስት ያካተተ መሆን አለበት (የሙያ ትምህርት የምስክር ወረቀቱ በአገር አቀፍ ተቀባይነት ያለው ሲሆን በVCE ፕሮግራም ውስጥ የተካተተ ይሆናል)። ይሁን እንጂ በዚህ ላይ ማተኮር ወይም የሆነ የVET ምስክር ወረቀት ማጠናቀቅ ላይኖርብዎት ይችላል። ለምሳሌ፣ የVCAL ፕሮግራም ለማሟላት ከተለያዩ የVET ምስክር ወረቀት ክፍሎች ወይም አካላት ውስጥ በመምረጥ ሰፋ ባለ መስክ የሥራ ልምድ ማግኘት ይቻላል። በVET ፕሮግራም የሚቀርቡት የሙያ ዓይነቶች ብዛት ሲኖራቸው ይህም አውቶሞቲቭ፣ ምሕንድስና፣ የሕንጻት ሥራ፣ መስተንግዶ እና ችርቻሮ፣ የህዝብ ግንኙነት፣ IT/ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ እርሻ፣ የአትክልት ሥራ፣ በመጋዘን ውስጥ ሥራ እና የፀጉርና የውበት ሥራን ያካተተ ይሆናል።

### ክፍል/Strand 3 — ከሥራ ጋር በተዛመደ ችሎታ

የVCAL ፕሮግራም በሥራ ቦታ ላይ በመመደብ ውይም በትርፍ ሰዓት አፕረንቲስሽፕ/ትሬኒሽፕ ወይም ለሥራ ልምድ የሚረዳ ትምህርት በማቅረብ 'ለሥራ ብቁ የሚያደርግ ችሎታ' እንዲያገኙ ይረዳል። ለሥራ ብቁነት እንዲዘጋጁ የጥናቱን ክፍሎችና አካላት መማር ይችላሉ። ለምሳሌ፡ ስለጤና እና ደህንነት ሥራ ወይም ስለሥራ ቃለመጠይቅ የማድረግ ችሎታ ክፍለ ትምህርቶች ናቸው።

### ክፍል/Strand 4 - የግለሰብ የእድገት ችሎታ

በማህበረሰብዎ ወይም በት/ቤት ባሉ የፕሮጀክት እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንደ VCAL የትምህርት ፕሮግራም አንድ ክፍል በመቁጠር ተሳትፎ ያደርጋሉ። ይህም በቡድን የመሥራት ችሎታን እንዲያዳብሩ ይረዳዎታል። ለምሳሌ፡ ት/ቤትዎ ከአካባቢው ምክር ቤት ጋር በመተባበር የመናፈሻ ቦታዎችን ማጠናከር ይፈልግ ይሆናል። በዚህን ጊዜ የሚወስዱት ትምህርት በVCAL ላይ ነጥብ ሊያስቆጥር ይችላል።

## የVCAL ትምህርት የት ነው የምወስደው?

## የVCAL ትምህርት በጥሩ ውጤት ካጠናቀኩስ በኃላ ወደ ከፍተኛ ትምህርት መግባት እችላለሁ ወይ?

ከመደበኛ ት/ቤት በቀጥታ ወደ ዩኒቨርሲቲ መግባት ከፈለጉ፣ ምናልባት ለርስዎ የVCAL ፕሮግራም ምርጫ ጥሩ ላይሆን ይችላል። ተማሪዎች በቀጥታ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ለመግባት እቅድ ሲያወጡ የVCE ፕሮግራም በመውሰድ ከቪክቶሪያ ሶስተኛ ደረጃ ተቀባይ ማእከል/VTAC የመግቢያ/ENTER ማግኘት ይቻላል። የVCAL ትምህርት በከፍተኛ ደረጃ የሚወስዱ ከሆነ እና ዩኒቨርሲቲ መግባት ከፈለጉ አስተማሪዎን ወይም አማካሪዎን መጠየቅ ምክንያቱም አንድ ተማሪ የVCAL ከፍተኛ ምስክር ወረቀት ካለው በአንዳንድ ዩኒቨርሲቲዎች ለመግባት ተቀባይነት ይኖረዋል። ይሁን እንጂ አንድ ተማሪ ከት/ቤት በቀጥታ ዩኒቨርሲቲ ለመግባት የተለመደ አካሄዳ አይደለም። አንዳንድ ሰዎች በቴፍ/TAFE ተቋማት ውስጥ የሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮርስ በመውሰድ ወደ ዲፕሎማ ወይም ድሕረ ዲፕሎማ በመምራት በዩኒቨርሲቲ ለሚያካሂዱት ኮርስ ሊጠቅም ይችላል። በዚህ መንገድ መቀጠሉ ለVCAL ትምህርት ጥሩ አጀማመር ይሆናል።

## የVCAL ትምህርት ካጠናቀኩ በኃላ ምን ምርጫ ይኖረኛል?

VCAL ትምህርት በቴፍ/TAFE ተቋማትና በአሠሪዎች በኩል ተቀባይነት ያለው ሲሆን ከሥራ ጋር በተያያዘ ተግባራዊ የሆነ ልምድና ችሎታን ለማዳበር ይረዳል። እነዚህ ችሎታዎች ከት/ቤት ወደ ሥራ ለመግባት፣ ከሥራ ጋር በተያያዘ ተግባራዊ የሆነ ልምድና ችሎታን ለማዳበር ይረዳል። እነዚህ ችሎታዎች ከት/ቤት ወደ ሥራ ለመግባት፣ ከሥራ ጋር በተያያዘ ሥልጠና ለማካሄድና በቴፍ/TAFE ተቋም በበለጠ ሥልጠና ለማድረግ ይረዳሉ።

በሌላ በኩል የVCAL ፕሮግራምዎን በ11ኛ ክፍል እያሉ ከመሰረታዊ ደረጃ ከጀመሩና በጥሩ ውጤት ከጨረሱ በኃላ በVCAL ፕሮግራም 12ኛ ክፍል ሆነው የመካከለኛ ደረጃን ወይም የከፍተኛ ደረጃን ማጠናቀቅ ይችሉ ይሆናል። እንዲሁም ያለዎን አማራጭ በመጠቀም ወደ ዩኒቨርሲቲ ለመግባት መወሰን እና ወደ የVCE ፕሮግራም መቀየር ይሆናል።

## ወደ ንግድ ዓለም እንድገባ VCAL ፕሮግራም ይረዳኛል ወይ?

የVCAL ፕሮግራም ካጠናቀቁ በኃላ ለንግድ ወይም ለኢንዱስትሪ ሥራ ብቁ የሚያደርግ የምስክር ወረቀት በማግኘት ስለጤና እና ደህንነት ሥራ (OH&S) በተመለከተ እውቀት ይኖርዎታል። ለሥራ ብቃት የሚሰጥ ትምህርት/አፕረንቲስሽፕ ወይም ሥልጠና/ትሬኒሽፕ በሚያካሂዱበት ጊዜ ይህ ቅድሚያ ያለው ትምህርት ግምት ውስጥ በማስገባት ዋጋ ይሰጠዋል።

ስለVCAL ፕሮግራም በበለጠ ማብራሪያ ለማግኘት በቪክቶሪያ ስራአተ ትምህርትና ጥናት ባለሥልጣን በስልክ 1800 134 197 መደወል ወይም በዌብሳይት፤ www.vcaa.vic.edu.au ላይ ማየት።